በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት
**መስተዳደር ምክር ቤት**
Benishangul Gumuz Regional State
ADMINISTRATIVE COUNCIL

ቁጥር/Ref,No. 379/[illegible]
ቀን/Date 29/04/2016

**ለክልሉ ጤና ቢሮ**
አሶሳ፣

**ጉዳዩ:- የፀደቀ መመሪያ ስለመላክ፣**

የክልሉ መንግሥት መስተዳድር ም/ቤት (ካቢኔ) ታህሣሥ 18 ቀን 2016 ዓ.ም ባካሄደው መደበኛ ስብሰባው ከቢሮው በቀረበው የጤና ባለሙያዎችን የጤና እና የምግብ ተቋማትን ምዝገባና የሙያ ሥራ ፈቃድ አሰጣጥ ክፍያን ለመወሰን በወጣው የኢንስፔክሽን ረቂቅ መመሪያ ላይ በስፋት በመወያየት አፅድቋል፡፡

ስለዚህ በውሣኔዉ መሠረት መመሪያ ቁጥር 064/2016 ተብሎ የተመዘገበ መሆኑን እያሳሰብኩ፣ ለአፈፃፀም ያመች ዘንድ የፀደቀውን መመሪያ 1 (አንድ) ጥራዝ በዚህ ሸኚ ደብዳቤ አባሪነት መላኩን አስታውቃለሁ፡፡

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት መስተዳድር ም/ቤት
The BGRS Administrative Council

ከሠላምታ ጋር

አሻድሊ ሀሰን እልእ[illegible]
ርዕሰ መስተዳደር

**እንዲያውቁት**
- ለክቡር ም/ርዕሰ-መስተደድር
- ለርዕሰ-መስተዳድርና ካቢኔ ጉ/ጽ/ቤት
- ለህግ ዘርፍ አማካሪ
- ለኢኮኖሚና ፋይናንስ አማካሪ
- ለአጀንዳ ውሣኔ ዝ/ሥ/ክ/ዳ/ዳይሬክተር
  በጽ/ቤቱ፣

**ግልባጭ**
- ለክልሉ ፋይናንስ ቢሮ
  አሶሳ፣

ስልክ/Tel-☎ 057-7750-218
ፋክስ/FAX 057-775-08-41/08-38
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box-[illegible] 44

ቤኒሻንጉል - አዲስ:ር የተስፋ አድማስ !!
Benishangul - A New Horizon of Hope
Email : BGRSAC@gmil.com

# በቤ/ጉ/ክ/መ/ጤና ቢሮ

# የጤና ባለሙያዎችን የሙያና ምዝገባ ስራ ፈቃድ፤የጤና እና ጤና ነክ፤የምግብና መጠጥ እና የምግብ ምርት ተቋማትን የብቃት ማረጋገጫ ስራ ፈቃድ አሰጣጥ ክፍያን ለመወሰን የወጣ የኢንስፔክሽን መመሪያ

ታህሳስ 2016 ዓ.ም

<u>አሶሳ</u>

## መመሪያ ቁጥር 064/2016 ዓ.ም

### የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የጤና ባለሙያዎችን የሙያና ምዝገባ ስራ ፈቃድ፤ የጤና እና ጤና ነክ፤የምግብና መጠጥ ተቋማትን የብቃት ማረጋገጫ ስራ ፈቃድ አሰጣጥ ክፍያን ለመወሰን የወጣ የኢንስፔክሽን መመሪያ ቁጥር 064-/2016 ዓ.ም

የጤና ባለሙያዎችን የሙያና ምዝገባ ፈቃድ፤ የጤናና ጤና-ነክ፤ የምግብና መጠጥ እንዲሁም የምግብ ምርት ተቋማትን የብቃት ማረጋገጫ ስራ አዲስ ፈቃድ ከማውጣታቸው ወይም ከማሳደሳቸው በፊት የአገልግሎት አሰጣጥ ክፍያ መክፈል ያለባቸው በመሆኑ፤

የአገልግሎት ክፍያ ተመን እና የአስተዳደራዊ መቀጮ ወሰን የክልሉ አከባቢ ወቅታዊ ሁነታ ታሳቢ በማደረግ ተገልጋዮችን ወይም የአገልግሎት ፈላጊዎችን የመክፈል አቅምን ያገናዘበ በመሆኑ፤

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የምግብ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥርን ለመወሰን የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 168/2016 አንቀፅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቅጽ 22 መሰረት ይህ የክፍያ መመሪያ ተዘጋጅቷል።

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌ

## አንቀጽ 1

## አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የጤና ባለሙያዎችን የሙያና ምዝገባ ፈቃድ፣የጤናና ጤና-ነክ እንዲሁም የምግብና መጠጥ ተቋማትን የብቃት ማረጋገጫ ስራ ፈቃድ አሰጣጥ ክፍያን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 168/ 2016 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## አንቀጽ 2

## ትርጓሜ

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥርን ለመወሰን የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 168/2016 አንቀፅ 2 ፣በኢትዮጵያ የምግብና የመድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀፅ 2 ስር ለተቀመጡ ቃላት የተሰጡ ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በዚህ መመሪያ ዉስጥ:-

1. "የጤና ባለሙያ" ማለት የሰውን ጤና ለመጠበቅ ወይም አገልግሎት ለመስጠት የክልሉ የጤና ተቆጣጣሪ እንደ ጤና ባለሙያ የተመዘገበ ሰው ነው፣
2. "የጤና ተቋም" ማለት የጤና አገልግሎት የሚሰጥባቸው እንደ ክሊኒክ፣ ጤና ጣቢያ፣ ሆስፒታል እና የመሳሰሉት ተመዝግበው ፈቃድ የተሰጣቸው ተቋማትን ይመለከታል፣
3. "የምግብ ተቋም" ማለት ማናቸውም የምግብ ምርት የሚቀነባበርበት ወይም የሚመረትበት፣ በጅምላና በችርቻሮ የሚችረችረበት፣ የምግብ አገልግሎት የሚዘጋጅበትና ምግብ የሚሸጥበት እንደ ሆቴሎች፣ ምግብ ቤቶች፣ ባርና ሬስቶራንቶችና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፣
4. "የጤና-ነክ ተቋም" ማለት እንደ የዉቤትና ሳሎን፣ የህጻናት ማቆያ፣አልጋ ወይም መኝታ ቤቶች፣ ት/ቤቶች፣ የመንግስት መ/ቤቶች እና የመሳሰሉት ለህብረተሰቡ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን ይመለከታል፣

5. “የመድሐኒት ተቋም” ማለት ህጋዊ ፈቃድ የተሰጠው ተቋም ሆኖ መድሀኒት በችርቻሮ የሚሸጥባቸው እንደ ገጠር መድሀኒት ቤት፣ መድሀኒት መደብር ፋርማሲና የመሳሰሉትን ተቋማቶችን ይመለከታል፤

6. “የአገልግሎት ክፍያ” ማለት አንድ የጤና ባለሙያ ወይም ከላይ የተዘረዘሩት ተቋማት ፈቃድ ሲያወጡ ወይም ሲያስድሱ ለተሰጣቸው አገልግሎት ህጋዊ ባለው ሰነድ (ካርኒ) ተቆርጦ ለመንግስት ገቢ የሚደረግ ገንዘብ ነው፤

## አንቅጽ 3.
## የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በክልሉ ወሰን ውስጥ በጤና ባለሙያዎች፤ በጤናና ጤና-ነክ እንዲሁም በምግብና መጠጥ ተቋማት እና ለህብረተሰብ በሚቀርብ ቁጥጥር በሚደረግበት የምግብ፣ መድኃኒት፣ የውበት መጠበቂያ ምርት፣ ህክምና መሳሪያ፣ የትምባሆ ምርት ተቋማት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## አንቅጽ 4.
## ዓላማ

የጤና ባለሙያዎችን የሙያና ምዝገባ ፈቃድ፤ የጤናና ጤና-ነክ፤ የምግብና መጠጥ ተቋማትን እንዲሁም የምግብ ምርት ተቋማትን የብቃት ማረጋገጫ ስራ ፈቃድ አዲስ ፈቃድ ከማውጣታቸው በፊት ወይም ከማሳደሳቸው በፊት ለሚያገኙት አገልግሎት ክፍያ እንዲከፈል ማድረግ ነዉ፡፡

## ክፍል ሁለት
## መሰረታዊ ድንጋጌዎች
## አንቅጽ 5

## የሙያና ምዝገባ እና የብቃት ማረጋገጫ ስራ ፈቃድ አስፈላጊነት

የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል ይቻል ዘንድ ማናቸዉም የጤና ባለሙያዎች የሙያና ምዝገባ ፈቃድ፤ ጤናና ጤና ነክ ተቋማት፤ የምግብና መጠጥ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት እና የምግብ ምርት ተቋማት መስፈርት ስለማሟላታቸው በቅድሚ ፈቃድ ቁጥጥር ሳይረጋገጥ እንዲሁም የብቃት ማረጋገጫ ሳያገኙ በየዘርፋቸው ተሰማርተው አገልግሎት መስጠት እንደማይችሉ እና በጤናና ጤና ነክ ተቋማት የሚሰጠው

አገልግሎት በምግብና መድኃኒት ምርት ደህንነትና ጥራት እና በአግልግሎት ብቃት ችግር ምክንያት በተገልጋይ ማህረሰብ ላይ ከፍተኛ የሆነ የጤና ችግር እንዳያስከተል ለመከላከልና ለመቆጣጣር ማናቸውም የጤና ባለሙያ፣ የጤናና ጤና-ነክ፤ የምግብና መጠጥ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እና የምግብ ምርት ተቋማት በተቀመጠዉ ስታንዳርድ መስፈርት መሰረት ተገቢውን ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት ለተገልጋይ ማህበረሰቡ እንዲሰጡ የስራ ፈቃድ እንድኖራቸዉ የወጣዉ የክልሉ ደንብ ስለሚያሰገደድ ነዉ፡፡

## አንቅጽ 6

## ጤና ባለሙያዎች የሙያ ስራ ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ስላለባቸው መስፈርቶች

ማንኛውም ሰው በጤና ሙያ ለመሰማራትና የሙ-ያ ስራ ፈ.ቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡-

1. ጤና ባለሙያዉ የተዘጋጀ የሙያና ምዝገባ ፈቃድ ጥያቄ ፎርም ማሙላት፤
2. ጤና ባለሙያው ከተመረቀበት ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ የተሰጠ የተማረውን የትምህርት ዓይነትና ትምህርቱን ስለማጠናቀቁ የሚገልፅ አግባብ ያለው ማስረጃ (ሰረተፊኬት፣ ዲፐሎማ፣ ዲግሪ፣ ትራንስክሪፕት)፤
3. ለጤና ባለሙያ የሙያ ብቃት ምዘና እንዲወስዱ ለተመረጡ የሙያ ዘርፎች የሙያ ብቃት ምዘና ያለፈ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰርተፍኬት፤
4. ሶስት ወር ያላለፈውና ባለሙያው ሙያውን ለማከናወን በሚያስችል የጤና ሁኔታ ላይ እንዳለ የሚያረጋግጥ የህክምና ምርመራ ምስክር ወረቀት ዉጤት ማቅረብ
5. የሁለት ፓስፖርት መጠን ፎቶግራፍ፤
6. የቀበለ መታወቂያ ኮፒ፤እና
7. የአገልግሎት ክፍያ የከፈለበት ደረሰኝ፡፡

## አንቅፅ 7

## የጤናና ጤና ነክ የብቃት ማረጋገጫ ስራ ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ስላለባቸው መስፈርቶች፤

ማንኛውም ሰው/ተቋም የጤና እና ጤና-ነክ፤ የምግብና መጠጥ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት፤ የምግብ ምርት አቅነባባሪ፤ጅምላ እና ችርቻሮ፤ የወቤት መጠበቂያ ወይም ኮስሞቲክስ ምርት እና የትምባሆ ምርት ጅምላና ችርቻሮ ተቋማቶች የብቃት ማረጋገጫ ስራ ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡-

1 ማንኛዉም ሰዉ/ተቋም ህጋዊ ማመለከቻ ወይም ደ/ቤ ከተቋሙ ያቀርባል፤

2 የብቃት ማረጋገጫ የሚያወጣ ሰዉ ወይም ባለሙያው ከተመረቀበት ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ የተሰጠ የተማረውን የትምህርት ዓይነትና ትምህርቱን ስለማጠናቀቁ የሚገልፅ አግባብ ያለው ማስረጃ (ሰረተፊኬት፣ ዲፕሎማ፣ ዲግሪ፣ ትራንስክሪፕት)፤

3 ተቋማቱ አስፈላጊ የሆነ መስፈርት ስለማሟላታቸው ያቀረቡት ዶኩመንት የተሟላ ስለመሆኑ እንዲሁም ቅድመ ወይም ድህረ ኢንስፔክሽን ተሰርቶላቸው ያሟሉ ስለመሆኑ፣

4 ሶስት ወር ያላለፈውና ባለሙያው/ሠራተኛዉ ሙያውን ለማከናወን በሚያስችል የጤና ሁኔታ ላይ እንዳለ የሚያረጋግጥ የህክምና ምስክር ወረቀት፤

5 የምግብ ተቋማት ከሆነ ደግሞ የህክምና የላቦራቶሪ ምርመራ ውጤት ማቅረብ፣

6 ሁለት ፓስፖርት መጠን ፎቶ ግራፍ፤ እና

7 የአገልግሎት ክፍያ የከፈለበት ደረሰኝ፡፡

## ክፍል ሶስት

## አንቅጽ 8

## የአገልግሎት እና ኢንስፔክሽን ክፍያ ስለማስከፈል

1. የአገልግሎት ክፍያ መጠን የሚወሰነው የጤና ባለሙያ ከሆነ ባለሙያው ያለውን የትምህርት ደረጃን መሰረት ያደረገ ይሆናል፡፡
2. የምግብ ወይም የጤና ተቋም ከሆነ ደግሞ የተቋሙን ዓይነት (ጤና ተቋም፣ ምግብ ተቋም፤ ሌሎች ጤና ነክ ተቋም እና ደረጃቸውን መሰረት በማድረግ የሚወሰን ይሆናል፣
3. ለአዲስ ወይም ለእድሳት የሚደረግ የባለሙያ ወይም የተቋም ክፍያ መጠን በቀረበዉ ጥያቄ መሰረት አግባብ ይፈጸማል፡፡

## አንቅጽ 9

## የጤና ባለሙያዎች የሙያና ምዝገባ ፈቃድ ስለማሳደስ

1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ የተሰጠውን የሙያ ፈቃድ በየሶስት ዓመቱ ማሳደስ አለበት፡፡
2. ማንኛውም የጤና ባለሙያ የተሰጠውን የሙያ ስራ ፈቃድ የጊዜ ገደብ ከመጠናቀቁ አንድ ወር በፊት የእድሳት ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡
3. ለሙያ ፈቃድ እድሳት የሚያመለክት ባለሙያ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡
   ሀ )በመንግስት ቤት የሚሰራ ጤና ባለሙያ የሙያ ብቃትና ስነ ምግባር ሁኔታን የሚገልጽ ከሚሰራበት ተቋም አግባብ ባለው ኃላፊ የተጻፈ የስራ ልምድ ማቅረብ፤

ለ )በግል ጤና ተቋም የሚሰራ ባለሙያ ከሆነ የሙያ ብቃትና ስነ ምግባር ሁኔታን የሚገልጽ ከሚሰራበት ክሊንክ፣ ከወረዳዉና ከዞን ጤና ተቆጣጣሪ አካል ወይም አገባብ ባለው ኃላፊ የተጻፈ የስራ ልምድና መለቀቂያ እንዲሁም የስራ ግብር ለመንግስት የከፈለበት የሚገልፅ ማስረጃዎችና አባሪ ደ/ቤ ከገቢዎች ማቅረብ አለበት፣

ሐ )ከዚህ በፊት የተሰጠዉ የሙያና ምዝገባ ፈቃድ ኦሪጅናል ማቅረብ፣

መ )ለጤና ባለሙያ ፈቃድ በህጉ ላይ የተቀመጠውን ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ መውሰዱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፣

ሠ )ሶስት ወር ያላለፈው ሙያውን ለማከናወን በሚያስችል የጤና ሁኔታ ላይ እንዳለ የሚያረጋግጥ የህክምና ምስክር ወረቀት፣

ረ ) ሁለት ፓስፖርት መጠን ፎቶግራፍ፣ እና

ሰ ) የአገልግሎት ክፍያ የተከፈለበት ደረሰኝ፡፡

4. ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም የስራ ልምድ ማለት በክፍያም ይሁን ካለ ክፍያ የሚሰጥ አገልግሎትን እንዲሁም መደበኛ እና የትርፍ ሰአት ስራን ያጠቃልላል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የተደነገገዉ እንደተጠበቀዉ ሆኖ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የሙያ ስራ ፈቃዱ ያላሳደሰ ባለሙያ ከሶስተኛው ዓመት መጨረሻ ቀን ቀጥሎ ባለው ቀን ጀምሮ ከእድሳት የአገልግሎት ክፍያው በተጨማሪ በየወሩ ለእድሳት የተቀመጠውን የክፍያ መጠን በፌደራል የጤና ባለሙያ ፈቃድ አሰጣጥና አስተዳደር ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 775/2013 መሰረት ቅጣት በመክፈል ለሚቀጥሉት ሁለት ወራት ማሳደስ ይችላል፡፡
6. የሙያ ስራ ፈቃዱ ያላሳደሰ ባለሙያ ከሶስተኛው ዓመት መጨረሻ ቀን ቀጥሎ ባለው ቀን ጀምሮ ከእድሳት የአገልግሎት ክፍያው በተጨማሪ በየወሩ ለእድሳት የተቀመጠውን የክፍያ መጠን ቅጣት በመክፈል ለሚቀጥሉት ስድስት ወራት ማሳደስ ይችላል፡፡
7. ማንኛውም ባለሙያ ተገቢውን ክፍያና ሌሎች መስፈርቶችን ካላሟላ የሙያና ምዝገባ ፈቃድ ማሳደስ አይችልም፡፡
8. ማንኛውም የጤና ባለሙያ ከተመዘገበበት የሙያ ስራ ወሰን ውጪ የጤና አገልግሎት መስጠት የተከለከለ ነው፡፡

## አንቀጽ 10

## የጤና እና ጤና ነክ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ስራ ፈቃድ ስለማሳደስ

1. ማናቸውም የጤና እና ጤና-ነክ፤ የምግብና መጠጥ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት፤ የምግብ ምርት አቅነባባሪ፤ጅምላ እና ችርቻሮ፤ የዉቤት መጠበቂያ ወይም ኮስሞቲክስ ምርት እና የትምባሆ ምርት ጅምላና ችርቻሮ ተቋማቶች በየዓመቱ ከሐምሌ-1 እስከ ነሐሴ 30 መካከል ባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ የብቃት ማረጋገጫ ስራ ፈቃድ ማሳደስ አለበት፡፡
2. ማንኛውም ተቋም የጤና ባለሙያ የተሰጠውን የስራ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የጊዜ ገደብ ከመጠናቀቁ አንድ ወር በፊት የእድሳት ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡
3. ማንኛዉም ተቋም የብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ ለማሳደስ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡-
   ሀ )ባለሙያዉ ከሚሰራበት ተቋም የተቋሙ የዓመታዊ የእድሳት ጥያቄ ደ/ቤ ከተሰራዉ የድህረ-ፈቃድ እንስፔክሽንጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፤
   ለ ) በተቆጣጣሪ ባለሙያዎች የተሞላ የእድሳት ኢንስፔክሽን ፎርማት መገምገም፤
   ሐ ) ለጤና ባለሙያዉ ሶስት ወር ያላለፈው ሙያውን ለማከናወን በሚያስችል የጤና ሁኔታ ላይ እንዳለ የሚያረጋግጥ የህክምና ምስክር ወረቀት፤
   መ ) በጤና ነክ ላይ የሚሰሩ ባለሙያዎች/ሠራተኞች የላቦራቶሪ ምርመራ ዉጤት ማቅረብ አለባቸዉ፡፡
   ረ ) ሁለት ፓስፖርት መጠን ፎቶግራፍ፤ እና
   ሠ ) የአገልግሎት ክፍያ የተከፈለበት ደረሰኝ፡፡
4. በንኡስ አንቀጽ-1 እና 2 በተገለጸው መሰረት ማንኛውም የጤና ተቋም የተሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ ስራ ፈቃድ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ሳያሳድስ ቆይቶ በመስከረም ወር ለማሳደስ ከመጣ (ከመስከረም 1 እስከ መስከረም 30 ባሉት ቀናት መካከል ለማሳደስ ከመጣ የዓመታዊ ክፍያውን 50% በመጨመር እንዲሁም ከጥቅምት 1 እስከ ጥቅምት 30 ባሉት ቀናት ከመጣ ደግሞ በዓመታዊ ክፍያው ላይ 100% ጭማሪ ክፍሎ በመጨረሻ ማስጠንቀቅያ የብቃት ማረጋገጫዉ የሚታደስ ይሆናል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ 4 የተገለጸዉን እንደተጠበቀዉ ሆኖ ማናቸዉንም ጤናና ጤና ነክ ተቋማት ከተጠቀሱት የተጨማሪ ቅጣት ጊዜ ገደብ አልፎዉ ሳያሳደስ የቀሩ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ስራ ፈቃዱ ይሰረዛል ወይም እንደተሰረዘ ይቆጠራል፡፡
6. ማንኛውም ባለሙያ ወይም ተቋም ተገቢውን ሌሎች መስፈርቶችን ካላሟላ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አይታደስም፡፡
7. ማንኛውም የጤና ባለሙያ ወይም ተቋም ከተመዘገበበት የሙያ ስራ ወሰን ውጪ የጤና አገልግሎት መስጠት የተከለከለ ነው፡፡

## ክፍል አራት

## አንቀጽ 11

## የአገልግሎትና ልዩ ልዩ የክፍያ ተመን

| የአገልግሎትና ልዩ ልዩ የክፍያ ተመን ሠንጠረዥ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች ዝርዝር | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | የአገልግሎት ክፍያ | |
| | | | ለአዲስ | ለእድሳት |
| 1. | **የምግብና መድኃኒት ተቋማት የብቃት ማረጋጫ ምስክር ወረቀት መስጠት** | | | |
| 1.1. | የምግብ አምራች ድርጅቶች<br>የዱቄት ፋብርካ፤የዘይት ፋብርካ፤ | በቢሮ | 8000 | 4000 |
| | ቁራ፤ባልትና ዉጤት መምረቻ፤አዮድን ጨዉ ድጋሚ ማሸግ፤የእንጅራ መጋጋሪያ፤አነስተኛ የዳቦና ኬክ መምረቻ፤ የተለያዩ ወፍጮ ቤቶች | በየደረጃው የሚገኙ የዞንና የከተማ ጤና መምሪያዎች ወይም ወረዳ ጤና ጽ/ቤቶች | 2000 | 1000 |
| 1.2. | የምግብ ምርት ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች (የአዮድን ጨዉ፤ የዘይት፤የስኳር፤ የዱቄት፤ ተለያዩ የታሸጉ ጅዉስ፤ታሸጉ የብስኩት፤የታሸጉ ዉኃዎች፤ ዓሳና የዓሳ ዉጤት፤የለስላሳ መጠጦች፤ ፤የአልኮል መጠጦች፤የወተትና ወተት ተዋፅኦ፤የፓስታና ሞኮሮኒ፤የእህል ፤ጥራጥሬ እና የቅባት እህሎች መሸጫ በረንዳ ቤቶች ወዘተ…) | በቢሮ እና በየደረጃው የሚገኙ የዞንና የከተማ ጤና መምሪያዎች ወይም ወረዳ ጤና ጽ/ቤቶች | 1500 | 600 |
| 1.3. | የምግብ ምርት ችርቻር ድርጅቶች<br>ኮከብ ሆተል ቤቶች | በቢሮ | 3000 | 1500 |
| | ኮከብ ያልሆኑ ሆተል ቤቶች፤ ሉካንዳ/ስጋ ቤቶች፤ቡና ቤቶች/Bar/፤ምግብ ቤቶች፤ባርና ሬስቶራንት፤ካፌ ቤቶች፤ከካፌና ሬስቶራንት፤ ግሮሴሪ ቤቶች፤ የሱፔርማርኬት ፤አተክልትና ፍራፍሬ/ጅዉስ/ ቤቶች እና የእህል መሸጫ በረንዳ ቤቶች | በዞንናና በከተማ ጤና መምሪያዎች ወይም ወረዳ ጤና ጽ/ቤቶች | 1200 | 600 |
| 1.4. | ኬክና ፓስቲን ቤቶች፤ቁርስ ቤቶች፤የጀበና ቡና መሸጫ ቤቶች፤ፈጣኝ ምግብ አቅራቢዎች (ቺብስ፤ሳምቡሳ)፤ | | 400 | 300 |
| 2. | **የመድሀኒት፤ህክምና መሳርያዎችና ላቦራቶሪ ሪኤጀንት ተቋማት የብቃት ማረጋጫ ምስክር ወረቀት መስጠት** | | | |

| ተ.ቁ | የአገልግሎትና ልዩ ልዩ የክፍያ ተመን ሠንጠረዥ | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የሚሰጡ አገልግሎቶች ዝርዝር | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | የአገልግሎት ክፍያ | |
| | | | ለአዲስ | ለእድሳት |
| 2.1. | የገጠር መድኃኒት ቤት | በቢሮ | 1200 | 600 |
| 2.2. | የመድኃኒት መድበር | | 1800 | 900 |
| 2.3. | የመድኃኒት ቤት | | 2200 | 1100 |
| 2.4. | የመድሀኒት እና የህክምና መገልገያ መሳርያዎች ጅምላ | | 6000 | 3000 |
| 3. | የውበት መጠበቂያ፣የንጽህና መጠበቂያና ዲተርጀንት ምርት ችርቻሮ ተቋማት ማረጋጫ ምስክር ወረቀት መስጠት | | | |
| 3.1. | የውበት መጠበቂያ፣ የንፅህና መጠበቂያና ዲተርጀንት ምርቶች አስመጪ፣ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች | በየደረጃው የሚገኙ የዞንና የከተማ ጤና መምሪያዎች ወይም ወረዳ ጤና ጽ/ቤቶች | 2000 | 1000 |
| 3.2. | የውበት መጠበቂያ፣ የንፅህና መጠበቂያና ዲተርጀንት ምርቶች ችርቻሮ ድርጅቶች | በየደረጃው የሚገኙ የዞንና የከተማ ጤና መምሪያዎች ወይም ወረዳ ጤና ጽ/ቤቶች | 1200 | 600 |
| 4. | የትምባሆ አስመጪ፣ አከፋፋይ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት | በቢሮ የም/መ/ጤ/ክ ዳይሬክቶሬት | 2400 | 1200 |
| 5. | የትምባሆ አስመጪ፣ችርቻሮ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት | በየደረጃው የሚገኙ የዞንና የከተማ ጤና መምሪያዎች ወይም ወረዳ ጤና ጽ/ቤቶች የም/መ/ጤ/ክ ዳይሬክቶሬት | 1500 | 1000 |
| 6. | የጤና ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት | | | |
| 6.1. | አጠቃላይ ሆስፒታል | በቢሮ የም/መ/ጤ/ክ ዳይሬክቶሬት | 2400 | 1200 |
| 6.2. | የተለያዩ ስፔሽያሊት ክሊኒኮች | | 2000 | 1000 |
| 6.3. | የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል | ዞን/ከተማ አስተዳደር የም/መ/ጤ/ክ ዳይሬክቶሬት | 1800 | 600 |
| 6.4. | ሪጅናል ላቦራቶሪ፣ደም ባንክ | በቢሮ የም/መ/ጤ/ክ ዳይሬክቶሬት›› | 1600 | 600 |
| 6.5. | ጤና ጣቢያ | የከተማ ጤና መምሪያዎች ወይም ወረዳ ጤና ጽ/ቤቶች | 1200 | 600 |
| 6.6. | መካከለኛ ክሊኒክ | በቢሮ እና በየደረጃው የሚገኙ የዞንና የከተማ ጤና መምሪያዎች ወይም ወረዳ ጤና ጽ/ቤቶች የም/መ/ጤ/ክ ዳይሬክቶሬት›› | 1200 | 600 |
| 6.7. | የመጀመሪያ ደረጃ ክሊኒክ | የዞንና የከተማ ጤና መምሪያዎችና ወረዳዎች የም/መ/ጤ/ክ ዳይሬክቶሬት›› | 600 | 200 |

| የአገልግሎትና ልዩ ልዩ የክፍያ ተመን ሠንጠረዥ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች ዝርዝር | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ | የአገልግሎት ክፍያ | |
| | | | ለአዲስ | ለእድሳት |
| 6.8. | ጤና ኬላ | ወረዳ ጤና ጽ/ቤቶች የም/መ/ጤ/ክ ዳይሬክቶሬት›› | 600 | 400 |
| 6.9. | ቤዚክ ላቦራቶሪ ወዘተ | በክልሉ የም/መ/ጤ/ክ ዳይሬክቶሬት | 1200 | 600 |
| 7. | የብቃት ማረጋጫ ምስክር ወረቀት መስጠት፤ እድሳት ማድረግ፣የስዉ ለውጥና ምትክ ብቃት ማረጋገጫ መስጠት፣ | | | |
| 7.1. | ኮስሞስትክስና ሌሎች | በየደረጃው የሚገኙ የዞንና የከተማ ጤና መምሪያዎች ወይም ወረዳ ጤና ጽ/ቤቶች የም/መ/ጤ/ክ ዳይሬክቶሬት›› | 600 | 400 |
| 7.2. | ትምባሆ ድርጅት ጅምላ አከፋፋይ | ቢሮ የም/መ/ጤ/ክ ዳይሬክቶሬት | 2400 | 800 |
| 7.3. | ትምባሆ ድርጅት ችርቻሮ | በየደረጃው የሚገኙ የዞንና የከተማ ጤና መምሪያዎች ወይም ወረዳ ጤና ጽ/ቤቶች የም/መ/ጤ/ክ ዳይሬክቶሬት›› | 1200 | 600 |
| 7.4. | የቴክኒካል ባለሙያ/የባለቤትነት/ ስም ለውጥ ለማድረግ | ›› | 600 | |
| 8. | የጤና ባለሙያ ምዝገባና ፈቃድ | | | |
| 8.1. | ዶክተሬት ዲግሪ | በስራ ሂደቱ | 400 | 200 |
| 8.2. | ማስትሬት ዲግሪ | በስራ ሂደቱ | 400 | 250 |
| 8.3. | የመጀመሪያ ዲግሪ | በስራ ሂደቱ | 308 | 250 |
| 8.4. | ሰርተፊኬት | በስራ ሂደቱ | 256 | 248 |
| 8.5. | ዲፕሎማ | በስራ ሂደቱ | 256 | 248 |
| 9. | ማናቸውንም የጠፋ ወይም የተበላሸ ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለመስጠት | በስራ ሂደቱ | 400 | 400 |
| 10. | አጠቃላይ የአገልግሎት ክፍያ (የድጋፍ ደብዳቤ፣ፋይል ማዛወር፣የመልቀቂያ ደብዳቤ ወዘተ..) ለመስጠት | በስራ ሂደቱ | 200 | |
| 11. | በድጋሚ ኢንስፔክሽን ለመስራት፡፡ | ከ7 ኪ.ሜትር በታች ከሆነ የትራንስፖርት እና የባለሙያዎች የምሳ ዓበል ከ7ኪ.ሜትር በላይ ከሆነ ደግሞ የትራንስፖርት እና የባለሙያዎችን ሙሉ አበልና የነዳጅ ወጭ ድርጅቱ የሚሸፍን ይሆናል፡፡ | | |

ክፍል አምስት

አንቅጽ 12

የመተባበር ግዴታ

የክልሉ ጤና ተቆጣጣሪ ይህን መመሪያ ለማስፈፀም እንዲችል ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

አንቀጽ 13

ተፈፃሚነት የማኖራቸው መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ህግ ወይም ልማዳዊ የአሰራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

አንቅጽዕ 14.

መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በክልሉ መስተዳደር ምክርቤት ከፀደቀበት ከታህሳስ 18 ቀን /2016 ዓ/ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አሶሳ ታህሳስ/18 ቀን 2016 ዓ/ም

አሻዲሊ ሀሰን አልአጀብ

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት

ርዕሰ መስተዳድር